# 30 days of prayer

# የ30 ቀናት ጸሎት

## A Prayer For Each Day
## For The Month



# አንደኛ ቀን - Day 1

‹‹እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፣የሚያሳጣኝ የለም በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፣ በረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል፡፡››
መዝ 23፡1-2

<<The lord is my shepherd, I lack nothing . He makes me lie down in green pastures ,he leads me beside quiet waters >> Ps 23:1

በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፣ አንተ የርህራሄ አምላክ ወደ አንተ የሚጮሁትን ሰምተህ የምትመልስ ነህና ፀሎቴን ወደ አንተ አቀርባለሁ፡፡ አንተ የተሰበረውን ልብ የምትጠግንና የሚያለቅሱትን የምታጽናና አምላክ ነህ፡፡

ጌታ ለተጠቁ መሸሸጊያ በመከራ ጊዜም መጠጊያ ነህ፣ ጌታ መልካም ነው በእርሱ የሚታመኑትንም ይጠነቀቅላቸዋል፡፡ ጌታ ሆይ በምናልፍባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ያንተን ልዩ ማጽናናት እንድትሰጠን እንለምንሃለን፣ በሞት ጊዜ፣ በመከራ ጊዜ፣ በመናወጥ ጊዜና በአስቸጋሪ ጊዜዎች ሁሉ መጽናናትን እንድታደርግልን እንለምንሃለን፡፡ አንተ በእኛ ሃዘን አትደሰትምና፣ ምህረትህ ከእኛ ጋር ትሁን በውስጣችን እንዲኖር አጽናኝህንም ላክልን፡፡ አዕምሮንም በሚያልፍና በአስደናቂው ሰላምህ ሙላን፣ ይህ ሰላምህ በመከራ ጊዜና በጭንቅ ጊዜ ደስታህን ይሞላብናል፡፡

ቅዱስ ስምህ የተባረከ ይሁን አይኖቻችን ሁሉ ወደ ማደሪያህ ቦታ ይመለከታሉ፣ ሐዘንና ሞት ወደ ማይገኙበት መንግስትህ እንመለከታለን፡፡ በዚያ ከአንተና ከአንተም መገኘት የተነሳ በማያቋርጥ ደስታ ውስጥ እንኖራለን፣ ፀሎቴን ሰምተሃልና ከልቤ በጣም አመሰግንሃለው ክብርና ምስጋና ለዘለዓለሙ ለአንተ ይገባሃል፡፡

# ሁለተኛ ቀን - Day 2

‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፣ ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች እንኳን ያለ እርሱ አልሆነም፡፡›› ዩሐ1፤1-3

<< In the beginning was the word, and the word was with God and the word was God. He was with God in the beginning . Through him all things were made without him nothing was made that has been made >> John 1:1-3

በሰማይ የምትሮር አባታችን ሆይ፣ የተቀደስክ ጌታዬ ሆይ ለአዲሱ ቀንና ስለአዲስ ዕድሎች አመሰግንሃለሁ፣ በዚህም ቀን የምጠይቅህን የወንድሞቼንና የእህቶቼን ፍላጎት እንድታሟላላቸው እንደመልካምነትህ ፣ አስደሳችነትህና ፍፁም ስለሆነው ፍቃድህና ለእያንዳንዱ እንደፍላጎቱ/እንደፍላጎቷ ልክ እንድታደርግላቸው እጠይቅሃለሁ፡፡ ጌታ ሆይ ነገ ይዞት ስለሚመጣው ጉዳይ ብዙ ጊዜ እንጨነቃለን፣ እንፈራለንም፡፡ አንተ ከእኛ ጋር ከሆንክልን ምንም አያስፈልገንም፣ ረሃብና ጥማት በክንፎችህ ስር አይኖሩም፡፡ አንበሳ ሊደክመውና ሊርበው ይችላል፣ ጌታን የሚፈልጉት ግን ከመልካም ነገር አይጎድሉም፡፡ ጌታ ሆይ አንተን መታመንና አንተም በምትሰጠን መርካትን አስተምረን፡፡ አንተም ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር እንዳለህና ከቶም እንደማትረሳን አሳውቀን፡፡ አንተ በሜዳ ላይ ያሉትን አበቦች እንኳን የምትጠነቀቅላቸው በመሆንህ እኛንም በእምነትና በመታመን ልባችንን ሙላው፡፡ ደካማውን እምነታችንን እንድታጠነክርልንና በአንተ ብቻ ጸንተን እንድንቆም እርዳን፡፡ ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የሕይወት ቃል አለህ አንተ የሕይወትና የበረከት ምንጭ ስለሆንክ በአንተ ላይ እንድንታመንና እ ንድንደገፍ እርዳን ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ቅዱስ ስምህ የተባረከ ነው አሜን፡፡

# ሶስተኛ ቀን - Day 3

ማቲዎስ 6፤24-34 አንብብ

Read Matthew 6:24-34

ሰማያት የአግዚአብሔርን ክብር ያውጃሉ የእጆችህንም ሥራ ያወራሉ፣ ከቀን ወደ ቀን ንግግርን ያበዛሉ ከሌሊት ወደ ሌሊት ዕውቀትህን ይገልጻሉ ሰዎች ግን ዘወትር በእምነታቸው ይወድቃሉ እግዚአብሔርን እንዲረዳቸው አልጠየቁምና ፈጣሪአቸውን መገንዘብ አይችሉም፣ ውስን በሆነው አዕምሮአቸውም እግዚአብሔርን መረዳትና መያዝ አይችሉም፡፡ ጌታ ሆይ ዛሬ የሕይወቴ ንጉሥ እንድትሆን እሻለሁ፡፡ የአንተን ክብር እንዳይ ከአንተ የሸፈነኝን መጋረጃ ከፊቴ አንሳው አንተ የውስጥ አካላቴን አበጅተሃቸዋልና ከእናቴም ማህፀን ውስጥ ጀምሮ ፈጥረሃቸዋልና፡፡ አስፈሪና አስገራሚ አድርገህ ሰርተኸኛልና አመሰግንሃለሁ፡፡ ሥራዎችህ እጅግ ግሩም እንደሆኑ ነፍሴ አውቃለች፣ አፈጣጠሬ ከአንተ የተደበቀ አልነበረም፣ በስውር ስትፈጥረኝ በአስገራሚና ግሩም በሆነ ጥልቀት በምድር ላይ ተፈጥሬአለሁ፣ ያልተፈጠሩትን እኔነቴን በአይኖችህ አየህ በመጽሐፍም ጻፍሐቸው ለእኔም የተፈጠሩት ቀኖች ገና ያልነበሩበት ወቅት ነበር አምላኬ ሆይ ሐሳብህ ለእኔ እንዴት ያማረ ነበረ ድምራቸውስ እንዴት የበዛ ነበረ ብቆጥራቸው ከባህር አሸዋ ይበዛሉ፡፡ ስነቃ ራሴንም ከአንተ ጋር አገኘሁት፣ ስለደግነትህ ላመሰግንህ እፈልጋለሁ መንገድህን አሳየኝ ከአንተ አጠገብ ለዘለዓለም ለመኖር እሻለሁና የግል ጉብኝት አድርግልኝ፣ በሕይወቴ አንተ ቀዳሚ ነህና ከልቤ ላገለግልህ እፈልጋለሁ፡፡

ዋጅተኸኛልና ኃጢያቴንም ይቅር ብለሃልና ወደፊትህ በእውነተኛ ንሰሐና ጽድቅህንም በመሻት እቀርባለሁ፡፡ ሁልጊዜም አንተ በእኔ ደስ እንዲልህ እሻለሁ አሜን፡፡

# አራተኛ ቀን - Day 4

‹‹በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁአን ናቸው መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና፡፡››ማቴ 5፤3

<< Blessed are the poor in spirit for theirs is the kingdom of heaven>> Matthew 5:3

የተአምራት ጌታ የሆንከ አምላኬ ሆይ፣ በዚህ ማለዳ በምስጋናና በረከትህን በሙላት ለማግኘት በፊትህ እቀርባለሁ፡፡ አዕምሮዬንና ልቤን አንተ በምትወደው መንገድ ቅረጸው፣ ልብህ እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት በሰማያትም ሁሉ አመስግኑት፣ ስለ ኃያሉ ሥራውም አመስግኑት፣ ጥልቅ ስለሆነው ትልቅነቱ አመስግኑት፡፡ ቅዱስና መለኮታዊ ቃልህንም እመገብ ዘንድ ጌታዬ ሆይ አዘጋጀኝ፡፡ ‹‹ሁለት ወይም ሶስት በስሜ በሚገኙበት ሁሉ እኔም በዚያ ከእነርሱ ጋር እገኛለሁ›› ጌታ ሆይ እፈልግሃለሁ፣ ፊትህንም እሻለሁ፣ አንተ የምታውቀንንና ፍላጎታችንን የምትረዳውን ያህል ማንም አያውቀንም፣ የፈጠርኸውን ሰብአዊ ማንነታችንን የምታረካ አንተ ብቻ ነህ፡፡ እንደ ፍቃድህና እንደ እቅድህ መሰረት ታበጀዋለህ በምስክሮችህም ጎዳና በሐብት እንደተሞላ እደሰትባቸዋለሁ፣ ምስክርነትህም የኔ ደስታ ናቸው ለእኔ ምክሮች ናቸው፡፡ በመንገዱ ሁሉ ነቀፌታ የሌለበት  የተባረከ ነው፡፡ እርሱ በእግዚአብሔር ህግ ይራመዳልና፣ የእግዚአብሔር ህግ ጽድቅ ነውና ፍርዱ ሁሉ ሕዝቦችን ይበልጣል  የተቀደሰ ስሙ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን አሜን፡፡

# አምስተኛ ቀን - Day 5

‹‹ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁአን ናቸው ይጠግባሉና፡፡››
ማቴ 5፤6

<<Blessed are those who hunger and thirst for Righteousness  for they will be filled >> Matthew 5:6

ዓሠለምን ሁሉ የምትቆጣጠር አምላኬ ሆይ ለአንተ ከልባችን እንድንገዛና ወደ አንተ እንድንቀርብ ዘወትር ባርከን፣ አምላኬ ሆይ ስለ ምህረትህ፣ ታማኝነትህ፣ ፍርድህና ደግነትህ አመሰግንሃለሁ፡፡ ስለ ታላቁ ፍቅርህም አመሰግንሃለሁ፡፡ ከጥልቁ ጥፋትም አውጥተህ ከጻድቃን ጋር አብረህ አስቀመጥኸኝ ለአንተ ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ ቃላት የሉኝም፣ ጌታ ሆይ እንዳንተ ያለ ማነው? በችሎታህ የሚያክልህ የለም ምህረትህም ከግምት ያልፋል፣ ምንም እንኳን በሃጢያቴ ባሳዝንህም ፍቅርህ ብዙ ነው ለእኔም መልካም የሆነውን ሁሉ ታስባለህ፡፡ ጸሎቴን ስማ መልስልኝም፣ አይኖቼንና ምልከታዬን ከፈትልኝ እውነተኛ አምላክ አንተ ብቻ ስለሆንህ አይኖቼ ወደ አንተ ናቸው፣ ሕይወቴን ሊያበላሹ ከሚችሉ ሐሰተኛ መናፍስት ጠብቀኝ፣ በዓለም ያለው ሁሉ ከአንተ እውነተኛ አምላክ ሊለዩኝ ይሻሉ፡፡ አድናቆት ሁሉ ይገባሃል፣ ክብርና ምስጋና ላንተ ነው፣ ስለ ዘለዓለማዊ ታማኝነትህ አመሰግንሃለሁ፡፡

# ስድስተኛ ቀን - Day 6

‹‹የሚምሩ ብፁአን ናቸው ይማራሉና››ማቴ 5፤7

‹‹Blessed are the merciful for they will be shown Marcy ›› Matthew 5:7

ጌታ ሆይ ሁል ጊዜ እናመሰግንሃለን፣ እናከብርሃለን ከፍ ከፍም እናደርግሃለን፣ አክብሮት ክብርና አድናቆት ሁሉ ለዘለዓለም ለአንተ ብቻ ይሁን፣ የማይገመተውን ፍቅርህንና ደግነትህን በዚህ ዘመን ለማስተዋል መበርታትን፣ ጸጋህንና ቸርነትህን ስጠን፣ ወደ አንተም አቅርበን፣ አንተን እናውቅ ዘንድ አይኖቻችንን ክፈት ይህ ዓለም ከወላጆቻችን ከማህበረሰቡ የወረስነውን እምነት ሰጥቶናል፣ በአዕምሮአችን አንተን እንድናስተውልና ምርጫችንም እንድናደርግህ እርዳን መንፈሳችንም ማዳንህንና ያለህን መንከባከብ ይረዳ ዘንድ እርዳን፣ በመፈለግ ብዛት ደክመን ሊሆን ይችላል፣ የዓለም ማታለል ብዙ መሰናክል ሆኖብናል፣ ከንቱ እምነትን መደገፍና የተሳሳቱ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ጊዜ ወስዶብናል፣ ጌታ ሆይ አዕምሮአችን ተከፍቶ እውነትን እንድንረዳ እርዳን፣ ስለስምህ ክብርና ስለመንግስትህ መስፋፋት ስትል አዕምሮአችንን አስፍተህ ግለጽልን፣ በዚህ የብርሃን ልጆች እንሆናለን፣ ይህ ብርሃን የሞቱትን ያስነሳል፣ ለደካሞች ኃይል ይሰጣል፣ መደገፍና ዋስትና ወደሞላበት ወደ ለምለሙ ሜዳህ በክንፎችህ ስር ውሰደን፣ አንተ ክብርና ምስጋና አክብሮት ሁሉ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይገባሃል፡፡

# ሰባተኛ ቀን - Day 7

‹‹የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡፡›› ዩሐ 6፤48

<<I am the bread of life >> John 6:48

ጌታዬን በትዕግስት ጠበቅሁት፣ ፊቱንም ወደ እኔ አዞረ ጩኸቴንም ሰማኝ፣ ከጭቃና ከአፈር ላይም አነሳኝ በአለትም ላይ አቆመኝ በጽናት የምቆምበትን ቦታ ሰጠኝ፣ በአፌም አዲስ መዝሙር አስቀመጠ፣ ለምስጋናውም ይሆናል፡፡ ብዙዎች ያያሉ ጌታንም ይፈራሉ፣ በእርሱም ይታመናሉ፣ በጌታ የሚታመን የተባረከ ነው፡፡ ወደ ትምክህተኛውና ወደ ውሸት ለሚያቀኑ አይመለከትም፡፡ አምላኬ ሆይ እምነቴ ባንተ ላይ ነው፣ የመንፈሳዊ ቤቴን የምመሰርትበት አለቴን ግለጽልኝ ይህም ተረጋግቼ እንድቆም፣ በወጀቡ ውስጥ ጸንቼ እንድቆም የአብርሃም፣ ይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ የሆንከውን እለምንሃለሁ፡፡ ሁሉን የሚበልጠውን ሰላምህን ስጠኝ፣ ታድነኝ ዘንድ ደስ ይበልህ፣ ትረዳኝም ዘንድ ፈጥነህ ና አንተን የሚሹ ሁሉ ደስ ይበላቸው፣ በአንተም ሐሴት ያድርጉ በማዳንህም ለሚታመኑ ሁል ጊዜ ‹‹ጌታ ታላቅ ነው ይበሉ›› እኔ ግን ደሃና ችግረኛ ነኝ ጌታዬ ያስበኝ አንተ ረዳቴና ነፃ የምታደርገኝ ነህ፣ አምላኬ አንተ ነህና አትዘግይ ደግና የምታፈቅር ስለሆንክ በአመጽ ደስ አይልህም፣ መንፈሴ የሚያስፈልገውን እንዲያገኝ እርዳኝ አንተ ፈውስና ፍቃድህን ለሕይወቴ ገልጸህ እንዲሳካልኝ እርዳኝ ወደ አንተ በመቅረብ ቅድስናህን ለማግኘት በቅድስናም ለመኖር እርዳኝ ዘለዓለም ይቅርታህን እንዳገኝ እርዳኝ ሌሎችንም ያለ ገደብ ይቅር እንድል አሳስበኝ መሃሪ አባት መሆንህን እንዳውቅና የአንተም ልጅ መሆኔን እንድረዳ በአንተም እንድደገፍ እርዳኝ አሜን፡፡

# ስምንተኛ ቀን - Day 8

‹‹በውኑ ሴት ከማህፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን ? እሳ ትረሳ ይሆናል እኔ ግን አልረሳሽም፡፡›› ኢሳ 49፤15
<<Can a mother forget the baby at her breast and have no compassion on the child she has borne ? Though she may forget , I will not forget you>> Isaiah 49:15

አምላኬ ሆይ ሕይወቴ በሁሉም መስክ የተመሰቃቀለ ነው፣ አንዳንዴ በመደነቅ በትክክለኛ አቅጣጫ እየተራመድኩኝ ነው ወይ? እላለሁ ቤተሰቤንስ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ማረፊያ እየመራሁ ነውወይ? አንተስ በእኔ ትደሰታለህ ወይ? ሌሎችም መልስ ላገኝላቸው የማልችላቸውን ብዙ ጥያቄዎችን እጠይቃለሁ፣ አንተ ግን ጭንቀቴንና ፍላጎቴን መስማትና ጸንቼም እንድቆም ከእኔ ጋር ትገናኝ ዘንድ ፈቅደሃል፡፡ አንተ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ ነህና ለነዚህ ጥያቄዎቼ መልስ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ፣ ወደ ሲኦል የሚወስደውን መንገድ መከተል ሳይሆን ወደ ዘለዓአለም ሕይወት የሚወስደውን ለማግኘት ከአንተ ቅርብ መሆንን እመርጣለሁ፣ ከዲያቢሎስና ከክፉ መናፍስት ጋር ለዘለዓለም እንዳላሳልፍ ከአንተ ጋር መሆንን እመርጣለሁ፣ ስለዚህ ወደ ራስህ አቅርበኝ፣ በዚህ ስቃይ በሞላበት ኑሮ እንዳላሳልፍ ተአምራቶችህ በሕይወቴ ይፈጸሙ፣ አድነኝም፣ ጉልበቴ የሆንከ ጌታዬ ሆይ እወድሃለሁ፣ እግዚአብሔር አለቴ፣ መሸሸጊያዬ ነፃም የሚያወጣኝ እርሱ ነው፡፡ በእርሱም እታመናለሁ የደህንነቴ ቀንድ ነውና ምስጋና የሚገባውን ጌታን እጠራለሁ፣ ከጠላቶቼም እድናለሁ፣ የሞት ጥላ ከበበኝ፣ የክህደት ማዕበልም አስፈራኝ የሲኦል ሕይወት ከበበኝ የሞት ወጥመድም ተደቀነብኝ፣ በጨነቀኝ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት ወደ እርሱም ጮኽኩ፣ እርሱም ከመቅደሱ ሰማኝ ጩኸቴም ወደ እርሱ ደረሰ ጆሮውም ሰማኝ አምላኬና አለቴ ሆይ መልስልኝ፡፡

# ዘጠነኛ ቀን - Day 9

‹‹ለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁአን ናቸው መንግስተ ሰማያት የነሱ ናትና››
ማቴ 5፤10

<<Blessed are those who are persecuted because of Righteousness for theirs is the kingdom of heaven >>
Matthew 5:10

የፍትህና የምህረት ምንጭ የሆንከ አምላኬ ሆይ ለልጆችህ ያለህ ፍቅር ወሰን የለውም፣ በፍቅርህ ስፋት የተነሳ መንፈስህን አፈሰስክብን፣ አንተ መልካምና ቸርነት የተመላህ አምላክ ነህና በቅዱስ መንግስትህ አባል አደረግኸኝ፣ ስለዚህ አዲስ ቀንና አዳዲስ ዕድሎች አመሰግንሃለሁ፣ አንተን በውስጤ እቀበልህ ዘንድ አእምሮዬን ሁለመናዬን ክፈትልኝ፣ ከሃጢያትና ከአለማዊ ምኞት ጠብቀኝ ፍቅርህንና መለኮታዊ መረዳትን በልቤ አድርግ ዕውር ነኝና ወደ አንተ መሰማሪያ እመጣ ዘንድ ምራኝ ልቤ በሰላም ያድግ ዘንድ ከጠማማነት አርቀኝ ሰለ ፍቅርህና መለኮታዊ እንክብካቤህ ልመንና አዕምሮዬን አድስ፣ ጻድቅ እንድሆንና አንተን በማወቅ በጽድቅ እንዳድግ እርዳኝ አንተን ከማወቅ የሚያግደኝን ግድግዳን ሁሉ አስወግድልኝ፣ ከጥርጣሬና ከሰይጣን የማለያየት ሙከራዎች ሁሉ ጠብቀኝ፣ ጌታ ሆይ ነገር ሁሉ ለበጎ ይሆንልኝ ዘንድ አድርግልኝ፣ ለአንተም ምስጋና፣ ክብርና አድናቆት ሁሉ ለዘለዓለም ይሁን አሜን!!

# አሥረኛ ቀን - Day 10

‹‹ከእነርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወርሳችሁ መልዕክት፤ እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት ፡፡›› 1ኛ ዩሐ 1፤5

‹‹God is light in him there is no darkness at all ››
1 John 1:15

ጌታ ሆይ የሰላም አምላክ ነህና ስለ ስጦታህ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፣ እነዚህ ስጦታዎችህ እንደ አለም ስጦታዎች ያልሆኑና ልቤንና እኔን እንደ ሃሳብና ፈቃድ የሚያዘጋጅ ናቸው፡፡ ጌታዬ ሆይ አንተ የፍቅርና የደግነት ሁሉ ምንጭ ነህ፣ የምህረትና የድጋፍ ምንጭ ነህ፡፡ ልቤን በፍቅርህ አእምሮዬንም በዕውቀት ሙላኝ፣ አዲስ ፍጥረትም አድርገኝ ይህም በሚገጥሙኝ ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ የሕይወትን መሰናክሎች ከአንተ ጋር ለማሸነፍ እችላለሁ፣ በእጆችህ ይዘኸኝና ደግፈኸኝ እነዚህን መሰናክሎች በድል ለማለፍ ያስችለኛል፣ እስከመንገዴ መጨረሻ ድረስ ከእኔ ጋር ተራመድ፡፡ አንተ መጠጊያዬና ደህንነት ነህ፣ ምስጋና ክብር አክብሮትና አድናቆት ሁሉ ለአንተ ይሁንልኝ አሜን፡፡

# አስራ አንደኛ ቀን - Day 11

‹‹ ለእናንተ የማስባትን ሃሳብ እኔ አውቃለሁ፣ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም ሃሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም ፡፡›› ኤር 29፤11
<< For I know the plans I have for you declares the lord , plans to prosper you and not to harm you, plans to give you hope and a future>> Jer 29:11

በአንተ ፊት ትሁት ሆኖ መገኘት እንዴት መልካም ነው፣ ከሌሎች ጋር በሚኖረን ሁሉ ትሁት ሆኖ መገኘት እንዴት ድንቅ ነው፣ በሕይወቴ ሁሉ ትሁት ሆኖ ለመገኘት እፈልጋለሁ ፀጋህን አብዛልኝ፣ ለአንተ ባለኝ ፍቅር ትሁት ሆኖ መገኘት እፈልጋለሁ፣ በዚህም ያለኝ ባህሪይ ሁሉ ከአንተ ጋር ይመሳሰልልኝ፡፡ ‹‹በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ቢፀልዩ ፊቴን ቢሹ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ እኔ ከሰማይ ሆኜ ፀሎታቸውን እሰማለሁ፣ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ፡፡›› ተብሎ ተጽፎአልና፣(2 ነገ 7፤14) በንፁህ ንስሐ ወደአንተ እንድመጣ እርዳኝ ወደ ኃላም በሐጢያት እንዳልመለስ በመንፈስህ ጠብቀኝ፣ ኃጢያቴን ብቻ በመርሳት አትተወኝም በጽድቅ እንድኖር ትረዳኛለህ የፀናው ፍቅርህ እጅግ በጣም ለእኔ ውድ ነው፣ ሰዎች በክንፎችህ ጥላ ስር መጠጊያን ያበጃሉ፣ በቤትህም ሃብት ይትረፈረፋሉ፣ ከወንዞችህ በረከት ታረካቸዋለን፣ ከአንተ ጋር የሕይወት ምንጭ አለና፣ በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን ለሚያውቁህ ፍቅርህ ዘወትር ይጨምር፣ ለሚያውቁህ የጽድቅ መንገድ ይሁንላቸው፣ ጌታ ሆይ ከወንዞችህ በሃብት እጠጣ ዘንድ ይገባኛል፡፡ ጌታ ሆይ ንፁሁ ምንጭህ በእኔ ውስጥ ለዘለዓለም ይፈስ ዘንድና ለሌሎችም በረከት እሆን ዘንድ ይገባኛል፣ ከሌሎች ጋር በሚኖረኝ ግንኙነት ፍፁም ትሁት መሆንን አስተምረኝ ትዕቢትን መተው ይሁንልኝ መስጠትንም ከመቀበል ይልቅ እንዳስብ እርዳኝ አሜን፡፡

# አስራ ሁለተኛ ቀን - Day 12

‹‹ እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እንወደዋለን ፡፡›› 1ኛ ዩሐ 4፤19

‹‹We love because he first loved us ›› 1 Jh 4:19

አምላኬ ሆይ በፍቅርህ ስለወደድከኝ አመሰግንሃለሁ፣ አስፈሪና ድንቅ ሆኜ እንድፈጠር አድርገኸኛልና አመሰግንሃለሁ፣ ሥራህ ግሩም ነው፣ ይህንንም ነፍሴ ታውቀዋለች፣ በሥልጣን ፈጠርኸኝ ነገር ግን ገና እየፈለግሁት ነው፣ ስለ ስምህ ክብር እጠቀምበት ዘንድ አንተው ምራኝ፣ እስከመጨረሻው ወደኸናልና የአንተም ፍቃድ ለእኛ ውጤታማ እንድንሆን ነው፣ በጉዞዬ ሁሉ ከእኔ ጋር ሁን ጌታዬ መርምረኝ ልቤንም እወቀው፣ ፈትነኝ ሐሳቤንም እወቅ ሐሳቤም እንደ ሐሳብህ እንዲሆን አድርግ፣ ‹‹ሐሳባችሁ እንደ ሐሳቤ አይደለም መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለም ጌታ ይላልና›› ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል መንገዴ ከመንገዳችሁ እንዲሁ የራቀ ነው፡፡ ከጥበብ ጋራ እለማመድ ዘንድ እለምንሃለሁ በዚህም በየዕለቱ በሚደረጉ ሥራዎች ለሌሎች የማካፍልበትን መንገድ አገኛለሁ፣ ለእናንተ የማስባትን ሐሳብ እኔ አውቃለሁ፣ ይህም ሐሳብ እንድትበለጽጉ እንጂ እንዲጎዳችሁ አይደለም፣ የወደፊታችሁ ሕይወትም እንዲያድግ ነው፡፡ እኔን ትጠራላችሁ ወደ እኔም ትፀልያላችሁ እኔም እሰማችኋለሁ እኔንም ትፈልጋላችሁ ታገኙማላችሁ፣ በሙሉ ልባችሁ ፈልጉኝ (ኤር 29፤11-14) ጌታ ሆይ ከልቤ እፈልግሃለሁ ለአለም ሁሉ የአንተን ፍቅር አስተላልፍ ዘንድ ወደ አንተ ፍቅር አቅርበኝ፣ በዘለዓለም መኖሪያህ ስፍራ አገኝ ዘንድና አክሊሎችህንም እቀበል ዘንድ በመዝገብህም ስሜ ይፃፍ ዘንድ የአንተ ወዳጅና ሰራተኛ አድርገኝ አሜን፡፡

# አስራ ሶስተኛ ቀን - Day 13

‹‹እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍፁም የሆነውን ያፀና ዘንድ አይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉና፡፡›› 2ኛ ዜና 16፤9

‹‹For the eyes of the Lord range throughout the earth to strengthen those whose hearts are fully committed to him›› 2 chr.16፤9

እግዚአብሔር ለተጠቁ ሁሉ ጽድቅንና ፍትህን ይሰራል እግዚአብሔር መንገዱን ለሙሴ አሳወቀ ስራውንም ለእስራኤል ህዝብ፤ ጌታ ሩህሩህና ደግ ነው ለቁጣ የዘገየ በፍቅርም ውስጥ የሚኖር ነው፡፡ እርሱ ሁል ጊዜ አይከስም ቁጣውንም ለዘለዓለም አያስቀምጥም እንደ ሃጢያታችን አላደረገብንም እንደ አመጻችንም አልከፈለንም ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እግዚአብሔር ለሚፈሩት ፍቅሩ ትልቅ ነው፡፡ ምስራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ መተላለፋችንንም ከእኛ አራቀው፣ አባት ለልጁ እንደሚያዝን እግዚአብሔርም ለሚፈሩት እንዲሁ ያዝንላቸዋል፡፡ እርሱ እንዴት እንደተሰራን ያውቃል፣ አፈርም እንደሆንን ያስባል፣ የሙታን ሕይወት እንደ ሳር ነው፣ እንደ ሜዳ አበባ ይለመልማል፣ ንፋስ ይነፍስበታል ወይንም ይጠፋል፣ የነበረበትም ቦታ አይታሰብም ነገር ግን የጌታ ፍቅር ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሚፈሩት ላይ ነው፡፡ ጽድቁም በልጅ ልጆች ላይ ነው ቃል ኪዳኑን በሚጠብቁትና ህጎቹን በሚያስታውሱ ላይ ክብሩ ይኖራል፡፡ ጌታ ዙፋኑን በሰማያት ዘርግቷል መንግስቱም ሁሉን ትገዛለች፡፡ እናንተ የጌታ መላዕክት የእርሱንም ሥራ የምትሰሩ ኃያላን ጌታን አመስግኑ፣ የሰማያት ሰራዊት ጌታን አመስግኑ፣ ፈቃዱንም የምታደርጉ ሁሉ አመስግኑት፡፡ በስልጣኑ ስር ያላችሁ ሁሉ አመስግኑት፣ ነፍሴ ሆይ ጌታን አመስግኚ፣ጌታ ሆይ መንገድህን አሳየኝ ኃጢያቴንም አስወግደው በጽድቅ መጎናጸፊያ ሸፍነኝ ለክብር መገለጫ መሳሪያ አድርገኝ ለብዙዎችም በረከትን ለማዳረስ ብቃት ስጠኝ አሜን፡፡

# አስራ አራተኛ ቀን - Day 14

‹‹ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁን ሆኖአል፣ አብ ሊሰግዱለት እንደዚህ ያሉትን ይሻልና፡፡›› ዩሐ 4፤23

‹‹Yet a time is coming and has now come when the true worshipers will worship the father in the spirit and in truth, for they are the kind of worshipers the father seeks›› John 4:23

በሰማያት የምትኖር አምላካችን ሆይ አንተ መልካም ነህና አመሰግንሃለሁ፣ እኔ የማይገባኝ ኃጢያተኛ ብሆን እንኳን ወደዚህ አለም መጥተህ አዳንከኝ ከእኛ ጋር እንድትሄድና እያንዳንዳችንን እንድትነካን እለምንሃለሁ፣ ይህ መንካትህ ነፍሳችንን፣ መንፈሳችንን፣ ስጋችንንም፣ይፈውሳልና አንተ ሁሉን ቻይ አምላክ ነህ ወደዚህ አምላክነትህ መልክ እንለወጥ ዘንድ የሚለውጠውን እስትንፋስህን በእኛ ላይ ላከው፣ ይህ መልክ ለሰው በፍቅርና በምህረት የሚሞላ ነውና፣ ይህም ባህርይ አንተ ሰዎችን በምታይበት አይን የማየት ዕድልን ይሰጠናል፣ ይህም ከአንተ ብቻ የሚወጣ እንጂ ከዚህ ዓለም ምኞት የሚወጣ አይደለም፡፡ ስለሁሉም አመሰግንሃለሁ፣ አንተ ብቻ ፈዋሽ ሁሉን አዲስ የምታደርግ አምላክ ነህ፣ ምንም የማይገባኝን ኃጢያተኛ አስበኸኝ ምህረትህን ስለአወረድክልኝ አመሰግንሃለሁ፣ የውስጣችንን ሕይወት የምትለውጥ አንተ ብቻ ነህ፣ ከእኔ የሆነ ምንም ነገር የለም የአንተ ሥራ ብቻ ነው፣ ስለ ሥምህ ክብርና ስለ መንግስትህ መስፋፋት ስትል የእኔን ሕይወት ተጠቀምበት ቅዱስ ሥምህ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን አሜን፡፡

# አስራ አምስተኛ ቀን - Day 15

‹ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የዋጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው፡፡››

ዩሐ 3፤13

‹‹No one has ever gone into heaven except the one who came from heaven the Son of Man›› John 3:13

ይህ ጊዜያዊ የሆነውን ሕይወት ሳስብ መልካም ሆኖ ይሰማኛል ያለፉትን ትውልዶች ስመለከት ሁሉም ሞተዋል፣ ተቀብረዋል፣ ነገር ግን አንድ ይመጣል፣ ይህ ቀን ሙታን ከሞት ተነስተው አንዳንዱ ወደ መንግስተ ሰማያት ሌሎች ደግሞ ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፡፡ የኔንም ሕይወት ከተባረኩት የትንሳኤ ተነሽዎች ጋር አድርግልኝ፣ ብዙ ሃይማኖቶች ቢኖሩም በአምላካችን ዘንድ ተቀባይነት ያለው ንፁህና ከስህተት የራቀው ግን ወላጅ የሌላቸውን ልጆችን መጠየቅና ራስንም ከአለም ርኩሰት መጠበቅ ነው፡፡ አንተን እንዳውቅና በጽድቅ የዘለዓለም ሕይወትን ወራሽ እድሆን ጸጋህን አብዝተህ ስጠኝ፣ ማንም ሊገራው የማይችለውን አንደበቴን መቆጣጠር እንድችል እርዳኝ፡፡ አንደበት ሊቆጣጠሩት የማይቻል ገዳይ መርዝን የተሞላ ሲሆን በእርሱ እግዚአብሔርን እንባርካለን፣ በእርሱም ደግሞ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎችን እንረግማለን፡፡ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ፡፡ አንደበቴ ሁልጊዜ መባረክን ብቻ ማውጣት እንድችል እርዳኝ፣ ከሰማይ የሆነውን ጥበብህን አብዛልኝና በአንተ ፍቃድ መመላለስን አስተምረኝ፣ በፊትህ ታዛዥ ሆኜ ለመኖር እችል ዘንድ ያንተ ጥበብ እንዲቆጣጠረኝና እንዲገዛኝ እለምንሃለሁ አሜን፡፡

# አስራ ስድስተኛ ቀን - Day 16

‹‹ከቃልህ የተነሳ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሳ ትኮነናለህ፡፡›› ማቴ 12፤37

‹‹For by your words you will be acquitted and by your words you will be condemned›› Matthew 12:37

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኝ ያደረገልሽንም አትርሺ ጌታ ኃጢትሽን ይቅር ይላል ደዌሽንም ሁሉ ይፈውሳል፣ እርሱ ሕይወትሽን ከጥፋት ያድናል፣ በፍቅርና በምህረቱ ያጎናጽፍሻል ወጣትነትሽንም እንደ ንስር ሊያድሰው በመልካም ነገሮችም ሊያረካሽ ይችላል፣ ላደረገልሽም በረከት ሁሉ ልታመሰግኚው ትፈልጊያለሽ? ወይስ ሁል ጊዜ በመማረር ለመኖር ትፈልጊያለሽ?

ሃሳብህን እንዴት ታካሂደዋለህ? ልቦናህን ቅን በሆኑ ነገሮች ትሞላለህን? ወይም ውስጣዊ የልብ ሰላምህ የአካባቢህን ሁኔታዎች ድል ለመንሳት ተዘጋጅተሃልን? ከእግዚአብሔር ጋር ታርቆ መኖር ብቸኛ መንፈሳዊ ሰላም የማግኘት ምንጭ ነው፣ አንዱ አሳዛኝ ነገር እኛ ወደ ሰማይ ሄደን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን አናገኝም ከሁሉ በፊት ወደ ሰማይ ሄደን መግባት አንችልም ነገር ግን እርሱ ወደ እኛ የመምጣቱና የምህረት እጁን ወደ እኛ የመዘርጋቱ መልካም ዕድል አለን፣ ይህንን እውነት ታምናለህን? ስለሆነም ወደዚህ መታረቅ መመልከት አለብህ ምክንያቱም እግዚአብሔር ምቹና ቀላል አድርጎልናል አንተ ማድረግ ያለብህ እርሱን መሻትና መፈለግ ብቻ ነው፡፡ አምላኬ ሆይ ልቤን ከአንተ ጋር ለማስታረቅና ዘወትር እንቅፋት የሆነውን የኃጢያትን ሕይወት ለመለወጥ ፈቃደኛ ነኝ፣ ይህን ሙሉ የሕይወት ሰላም ሊሰጥ የሚችለውን ዕድል በማግኘት የአንተን የተቀደሰ ሥም ዘወትር አመሰግናለሁ አሜን፡፡

# አስራ ሰባተኛ ቀን - Day 17

‹‹የእግዚአብሔር ፍቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍፁምም የሆነውን ነገር ምን እደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡›› ሮሜ 12፤2

‹‹Do not conform to the pattern of this world, but be transformed by the renewing of your mind then you will be able to test and approve what god's will is-his good pleasing and perfect will›› Romans 12:2

እግዚአብሔር ሆይ ለሰጠኸኝ መረዳት አመሰግናለሁ፣ አንተንና የአንተን መንገድ ለማወቅ እእምሮዬን ለማደስ የመንፈስ ቅዱስ ኃይልህን ስጠኝ በፀሎቴ ሁሉ የነቃሁ እንድሆን፣ በምመገበው ሁሉ የረካሁ እንድሆን በሥራዬ የታመንኩ እንድሆን፣ በፍላጎቴም የተስተካከልኩ እንድሆን እርዳኝ፣ በግንኙነቴም ሁሉ መልካም እንድሆን፣ በባህሪዬ ሰላማዊ፣ በንግግሮች ፈጣን፣ በባህሪዬ ቀጥተኛ እንድሆን እርዳኝ፡፡ ጌታ ሆይ ሐሳቤን፣ ንግግሬን፣ ተግባሬንና ጉድለቴን ሁሉ ለአንተ አቀርባለሁ፡፡ አንተን እንዳስብ ስለ አንተ እንድናገርና ለቃልህ በትጋት እንድሰራ እርዳኝ፣ ልቤን የአንተን ፍቅር በማሰብ፣ ክፋትን በመጥላት ምህረትህን ለወገኖቼ የአለምንም ነገሮች ሁሉ ለመጥላት እርዳኝ ስሜቴንና ፍላጎቶቼን በመስቀል አሸናፊ እንድሆን እርዳኝ፣ እንዲሁም ራስ ወዳድነትን በቸርነት፣ ቁጣንና ንዴትን በቅንነት፣ ቀዝቃዛነትን በነቃ አምልኮ እንድተካ እርዳኝ፡፡ በነገሮች ሁሉ ጠንቃቃ እንድሆን፣ በአደጋ ጊዜ ጎበዝ እንድሆን፣ በመከራና በችግር ጊዜ ጠንቃቃ እንድሆን፣ በውጤቴም የተቃናልኝ እንድሆን እርዳኝ፣ ጌታ ሆይ በሙሉ ልቤ አመሰግንሃለሁ፣ ክብር ሁሉ ለአንተ ይገባሃል አሜን፡፡

# አስራ ስምንተኛ ቀን - Day 18

አቤቱ እኔን ለማዳን ተመልከት፤ አቤቱ እኔን ለመርዳት ፍጠን፤መዝ 68፤703

"Make hasten O God to deliver me, make haste to help me O lord" Ps 70:1

ሰማይንና ምድርን የሠራህ ተአምራትን የምታደርግ ሰማያዊ አባት ሆይ አንተ የኃይልና የፍቅር ሁሉ ምንጭ ነህ፡ የስጦታዎች ሁሉ መነሻ ነህ፡፡ የአንተን መለኮታዊ ማንነት አሳየኝ፣ አንተን በጣም እፈልግሃለሁ፣ ምን እንደማደርግ ባላውቅም አይኖቼ በእንተ ላይ ናቸው፤ ምድር ሁሉ በክፉ፣ በጥላቻና በቂም የተሞላች ብትሆንም እኔ ግን የአንተን ፍቅር እሻለሁ፤ አንተ የማያልቅ የፍቅር ምንጭ ነህ፣ አንተ የሁሉ ነገር ፈጣሪ የሆንክ ብቸኛ አምላክ ነህ፤ እኛን የፈጠርከን ስለምትወደን እና መለኮታዊ እቅድህ የሆነውን የነፍሳችንን መዳን ለመፈፀም ነው፡፡ አሁንም እንፈልግሃለን፣ ከእኛ ጋር ና፤ እርዳንም በአንተም ብቻ የተሞላን አድርገን፣ በልዩ መቅረብህ ንካንና ነፍሳችንን ፈውሳት፣ ተአምራዊው ፈውስህ ከሃጥያት በፊት ወደነበረው ሰውነት እንዲለውጠን ታድሰናለህ፣ ፍቅርህን ወደሚያንጸባርቅ ወደማይወድቀውና ያለእርሱ መኖር ወደማንችለው ሰማያዊ ፍቅርህ አቅርበን፣ ሰዎችንም ሁሉ እንድንወድ አደርገን፣ አንተ በምታያቸው እይታ እኛም እንድናያቸው እርዳን፤ አንተም በጥላቻና በርግማን እንድታያቸው ሰይጣን መጥፎ ሁኔታዎችን በማስፋፋት ነፍሳትን ከድህነት ውጭ ለማድረግ እየሰራ ነው፤ አንተ ከሁሉ በላይ ኃያል የሆንክና ብድራታቸውንም እንደየስራቸው የምትከፍል ነህ፤ አንተ የኃይል እና የእውቀት ሁሉ አምላክ ነህ፤ለቸርነትህና ለደግነትህ ከልቤ አመሰግንሃለሁ፡፡ እኔ ደካማ ሰው ነኝ፣ ልቤን በጸጋህ ሙላው፣ በአንተም ብቻ የተሞላ አድርገው አሜን!!

# አስራ ዘጠነኛ ቀን - Day 19

‹የሚጨመር ሃሳብ አለ›

የዛሬው እለት በህይወትህ የመጨረሻዋ ቀን መሆንዋን ብታውቅ ምን ታደርጋለህ? የትኛውን የህይወት ባህሪ መለወጥ ትሻ ይሆን? ወይስ ወደመደበኛው የእለት ስርዓት ትሄድ ይሆን? ወይም ወደ እግዚአብሔር ቀርበህ ምህረቱን ትለምን ይሆን? ወይስ የቅርብ ቤተሰቦችህን ሰብስበህ ዜናውን ታሰማቸው የሆን? ያ ቀን አስተሳሰብህን ሁሉ የሚለውጥ የህይወት ጎዳናህም የተለየ አቅጣጫ የሚይዝበት ይሆናል፤ ልታውቀው የሚገባህ ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በዚህ አይነት ሃሳብ ውስጥ እንድትሆን የሚያበረታታህ ስለሆነ ጤናህና አቅምህ ደህና በሆነበት ሰዓት እንድታስበው ትጋት አድርግ፤ በዚህም ያለህን አቅምና ችሎታ ለእግዚአብሔር መንግስት አገልግሎት በማዋል ዘላለማዊ በረከቱን ለማግኘት መትጋት አለብህ፤ ምክንያቱም እግዚአብሄር ስለሚወድህ የተባረክ እንድትሆን ይሻል፤ ዋናው ጉዳይ ህይወትህን በሙሉ ለእርሱ እንድታቅርብ እና እርሱን የህይወትህ መሪ ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳን መለመን አለብህ፤ ጌታ ሆይ ቀሪ ግዜዬ በሙሉ የአንተን ስም ለማክበር እንዲሆንልኝና በመንፈስ ሕብረት እንዲኖረኝ፣ የአንተን ይቅርታ በሕይወቴ እንዲሞላኝ እርዳኝ፤ ለዚህም መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠኝ ቅድስና ታማኝነት በሙሉ ልቤ ከአንተ ጋር ለመጓዝና በሕይወት ዘመኔ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለመጓዝ ፈቃደኛ ነኝ አሜን!!

# ሃያኛ ቀን - Day 20

**‹የሚጨመር ሃሳብ አለ›**

እግዚአብሔር ሆይ ለእኔ ያለህ ሃሳቦች እንዴት ያማሩ ናቸው? ብቆጥራቸው ከባህር አሸዋ ይበልጣሉ፤ ስነቃ ሁል ግዜ ከአንተ ጋር ነኝ፣ ጌታ ሆይ ፈትነኝና ልቤን እወቅ፤ በስህተት መንገድ ከተገኘሁ ወደ ዘላለማዊ መንገድህ እንድመለስ ምራኝ፤ አንተ የሕይወት ውሃ አለህና፣ በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን፣ አንተን ለሚያውቁና ቀና ልብ ኖርዋቸው ፍርድህን ለሚጠባበቁ ምረትህን አብዛላቸው፤ ጌታ ሆይ የሕይወት አቅጣጫዬን እንዳውቅ እፈልጋለሁ፤ ጉዞዬስ ወዴት ነው? ወደ ዘለዓለማዊው መንገድ ነው ወይስ ወደ ጥፋት መንገድ? ወደ አንተ ጥበቃ እመጣ ዘንድም ዘለዓለማዊውን መንገድ አሳየኝ፤ የአንተን የህይወት በሮች አሳየኝ፤ ወደ ዘለዓለማዊ መንግስትህ አንድመጣ እና በአንተ መገኘት ሁልግዜ ሀሴትና ምስጋና ይሞላኝ ዘንድ መንገድህን አሳየኝ ጸሎቴን ስማ ስጮህም እኔን ለመርዳት ፍጠን፤ ሳለቅስ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብልና ስማኝ፣ እንደውጭ ሰው በአጠገብህ አኖራለሁ እንደአባቶቼም እንግዳ ሆኜ ኖሬአለሁ፣ የዘለዓላማዊ ሕይወትን እስካገኝና በሞትም ላይ ድልን እስካገኝ ደረስ ጽድቅህን ከሚሹ ጋር አብረህ ጠብቀኝ፤ ከእኔ ጋር ቅርብ ስለሆንክና ፀሎቴን ስለምትሰማ አመሰግንሃለሁ፤ በሕይወቴ ጣልቃ እንደምትገባና አዲስ የሕይወት ጅማሬ እንዲኖረኝ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ እንደምትሰጠኝ አምናለሁ፤ ምክንያቱም እኔ እንደ አንተ ሐሳብ ለመኖር እና በቅድስናህ መንፈስ ለመመራት ፈቃደኛ ነኝ አሜን!!

# ሃያ አንደኛ ቀን - Day 21

**‹የሚጨመር ሃሳብ አለ›**

የሰማይና የምድር ጌታ ሆይ ስለአዲሱ ቀንና አዳዲስ እድሎች አመሰግንሃሁ፤ በከፍታዎች የምትኖር አምላክ ሆይ ጩኸቴን ስማኝ እኔን ለመርዳት ፍጠን ጥርጣሬም አለኝና፣ አለምም ጠልቶኛልና የፍቅርን መልክ በፊቴ አበላሽተዋልና እለት በእለት ዓለም ስለአንተ እና ስለፍቅርህ የተሳሳተ ሃሳቦችን እያቀረበችልኝ ነው፤ የክፉ ሃሳብም ሀልጊዜ ሊያሳየኝ የሚሞክረው አንተ ከእኔ የራቅህ ኃጢአትም ጣፋጭ ነው ለማለት ያስቸግራል፤ ሰይጣን ከአንተ አርቆ ሊያቆየኝ ሁሉንም ዘዴዎች እየተጠቀመ ነው ከአንተም ርቄ እድቆይ የእኔን ደካማነትና ከእውቀት ማነስ ይጠቀማል፤ ነገር ግን አንተ እግዚአብሔር ከክፉው ሁሉ ድልን እንደሰጠኸኝና አባቴም እንደሆንክ አውቃለሁ፡፡ የክፉው መንፋስ ልጆቹን እንዲጎዳ አይፈቅድለትም፤አምላኬ ሆይ በመንፈስህ እንድትሞላኝ እና እኔም በሚትረፈረፈው ፍቅርህ እሞላ ዘንድ እፀልያለሁ፤ በዚህም አንተ እንዳስተማርካቸው ሌሎችን መቀበል እንድችልና ወንድሞችንም እህቶችንም በፍቅር እንድወዳቸውና እንድቀበላቸው እርዳኝ፤ አሜን!!

# ሃያ ሁለተኛ ቀን  - Day 22

**‹የሚጨመር ሃሳብ አለ›**

አምላኬ ሆይ ከልቤ አመሰግንሃለሁ፤ በዚህ ጊዜ ቀርቤ የምጠይቅህ የእኔን እና የቤተሰቤን ሕይወት እንድትመራ ነው፤ ጌታ ሆይ እረኛ እንደሌለን በጎች በዚህ ዓለም ጉስቁልና እየተሰቃየን ነው፤ሕብረተሰባችን ስለአንተ የሚያደናግሩ ሃሳቦችን ሲሰጠን ቆይቷል፤ አንተ ሁሉን የምትወድና ብዙ ፍቅርና ርህራሄን የተሞላህ ሆነህ ሳለህ እንደበቀለኛ አድርገው ያቀርቡሃል፤ ጌታ ሆይ ከጨለማው ባህር ወደ አስደናቂው ብርሃን ውሰደኝ፤ ይህ ብርሃን የወደቁትን የሚያነሳ የሞቱትን የሚቀሰቅስ ነው፤በመንገዴ ሁሉ እንድትመራኝና መንገድህንም እንድታስተምረኝ አለምንሃለሁ፤ ፍርድህን ተጠምቻለሁ ዓለም መጣልንና መወገድን ሰጠችኝ፤ የአንተ ስጦታ ግን ከዓለም የተለየ ነውና አማኝ እንድሆን እርዳኝ፤ አንተን እንዳውቅ ስለሰጠኸኝ እድል አመሰግናለሁ፣ ይህም ከአንተ ብቻ የተሰጠኝ እንደሆነ አምናለሁ፤ ስለምትወደኝም ይህንን እድል ሰጥተኸኛል፤የአንተ አላማ በሕይወት እንድኖርና ከጨለማ ባሕር እንድወጣ ነው፤ አባቴ ነህና የልብህ ፍላጎት የእኔ ተደስቶ መኖር ነው፤የአንተ ደስታ እኔ ወደአንተ እና ወደአንተ መልክ እንድለወጥ ነው፤ ጌታ ሆይ ሁልጊዜ ለአንተ ክብር ምስጋና ይሁን፡፡

# ሃያ ሶስተኛ ቀን  - Day 23

**‹የሚጨመር ሃሳብ አለ›**

ጌታ ሆይ በአንተ ሕይወቴ አምሮበታል፤ አንተ የፍትህና የምህረት ንጉስ ነህ፣ምህረትና ፍቅር የምትሰጥ፤ በንፁህ ልብና አምልኮ ለሚፈልጉህ ቅድስናን የምትሰጥ ነህ፤ የሕይወት ውሃ ምንጭ ነህና ከእርሱ ጠጥቼ እንድረካ አደረከኝ፤ ጌታ ሆይ መርምረኸኛልና ታውቀኛለህ፤ ስሄድና ስቀመጥ አንተ ታውቃለህ፤ሃሳቤን ገና ከሩቅ ታውቀዋለህ፤ ስሄድም ስተኛም ታውቀዋለህ፤ መንገዴ ሁሉ በአንተ የታወቀ ነው፤ ቃል ከአፌ ሳይወጣ አንተ ታውቀዋለህ፤ ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ ወይ ከአንተ መገኘት ወዴት ልሸሽ እችላለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፤ መኝታዬን በሲኦል ባደርግ አንተ በዚያ አለህ፤ ቀኖቼ መልካም ናቸው ምክንያቱም የአንተን ትዕዛዝ ለመከተል ፈልጌአለሁና መንገድህንም አስተምረኝ በጽድቅህም አሰልጥነኝ፤ ትዕዛዞችህ ከእኔ ጋር ናቸውና በአካባቢዬ ላሉት በረከት እሆን ዘንድ እርዳኝ ኃጢአትን ባደርግ የጽድቅ መነፈስህን በማሳዘኔ እፀፀታለሁ፤አንተ ግን ከኃጥያቴ በቶሎ ታወጣኛለህ፤ አበረታታኝ፣ ቁስሎቼንም ፈውስ፤ በዚያ ከበፊት ይልቅ ብርቱ እሆናለሁ፤ ቀኖቼን ለአንተ እጆች አስረክባለሁ፤ በውጤታማነቴም ይሁን በውድቀቴ አንተ ታጠነክረኛለህ፤ በድካሜና በውድቀቴም ግዜ ታጠነክረኛለህ፤ በእኔም የሕይወት ስኬት ትደሰታለህ፤ አሜን!!

# ሃያ አራተኛ ቀን - Day 24

**‹የሚጨመር ሃሳብ አለ›**

ጌታ ሆይ መርምረኸኛልና ታውቀኛለህ፤ ስቀመጥና ስነሳ ታውቃለህ፤ ሃሳቤንም ከሩቅ ታውቀዋለህ፤መንገዴም ሁሉ በአንተ ዘንድ የታወቀ ነው፤ ቃሌም ከአፌ ሳይወጣ ታውቀዋለህ፤ ከኋላዬ ትደግፈኛለህ፤ እጅህንም በእኔ ላይ ታኖራለህ፤ ይህ እውቀት ለእኔ እጅግ አስገራሚ ነው፤ እደርስበትም ዘንድ እጓጓለሁ፤ ወደ ጽድቅህና ቅድስናህ ሳበኝ፤ ሕይወቴ እንደእንፋሎት ነውና ትንሽ ታይቶ እንደሚጠፋ ያህል፤ ያለኝን ጊዜያቶች በሙሉ አንተን ለማወቅ ጉዳይ ላውለው እፈልጋለው፤ እስካሁንም በአኃጥያት ልምምድ ውስጥም ብሆን አንተ ግን ኃጥያቴን እንድታርቀውና ዘለዓለማዊ በረከትን እንድታለብሰኝ እመኛለሁ፤ ሁኔታዎች አስቸጋሪ ናቸውና አሁንም ወደ አንተ እጮሃለሁ፤ ጌታ ሆይ ሰምተህ መልስልኝ፤በስምህ እና በኃይልህ አድነኝ ፀሎቴንም አድምጥ፤ ልመናዬን ቸል አትበል ሰምተኽ መልስልኝ፤ ከጠላቴ ንግግር እና ከአመጸኞች ማስፈራራት የተነሳ ታውኬያለው፤ ተቸግሬአለሁ፤ መከራን እያመጡብኝ በብስጭት ያስጨንቁኛል፤ በልቤ ውስጥ ሀዘን አለ፤ የሞት ፍርሃት ከእኔ ላይ ወድቋል፤ ፍርሃት እና መደናገጥ ይዞኛል፤ አመጽ በእጅጉን ከቦኛል፤ እኔም የእርግብ ክንፍ ቢኖረኝ አልኩ፤ በርሬም ወደ እረፍት እሄዳለሁ፤ እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እጮሃለሁ፤ እርሱም ያድነኛል፤ በምሽት፣ በጠዋት፣ በቀትርም ቢሆን ብሶቴን እናገራለሁ፤ እርሱም ድምጼን ይሰማል፡፡

# ሃያ አምስተኛ ቀን - Day 25

‹ልበ ንፁሃን ብፁኣች ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና› ማቴ 5፤8
‹Blessed are the pure in heart for they will see God› Matthew 5፤8

የሰማይና የምድር ጌታ ተአምራትን ሁሉ የምታደርግ፣ ስለዚህ አዲስ ቀን አመሰግንሃለሁ፤ ስለሰጠኸኝ አዲስ እድልና የአንተን ቅድስና እንዳውቅ ስላደረከኝም አመሰግንሃለሁ፤ የእግዚአብሔር ቃል ሰዎቸን በአቀራረባቸው፣ በአዕምሮአቸው፣ በሃሳባቸውና በእውቀታቸው ዋጋ ይሰጣቸዋል፤ የአንተ ሃሳብና አመለካከት ከዓለም የተለየ ነውና አመሰግንሃለሁ፤ ጌታ ሆይ የሰው ዋጋ በልቡ መሆኑንና እንዴት በሕይወት እንደሚኖር አንተ ታውቃለህ፤ እውነተኛ ፍቅር ሰውን ሁሉ መውደድና አንዱን ከሌላው ሳይለዩ፣ አድሎ ሳያደርጉና ሌላውን ሳይጠሉ መሆኑን አንተ ታሳውቃለህ፤ ምንም እንኳን በኃጢአትና በአመጽ ውስጥ ብንገኝም እኛ ለአንተ ዋጋ ያለን ሰዎች አድርገኸናል፤ ምንም ነገር ቢሆን አንተ ልጆችህን ትወዳለህ፤ ጌታዬ ሆይ የማያልቀውን ፍቅርህን እንድናውቅና በእርሱም እንድናድግ እርዳን፤ አንተ እንዳለህ ፍቅርና ስጦታ ሁሉ እኛንም ለእርሱ እንድንኖር እርዳን፤ እያንዳንዳችን በአንተ መልካም ተምሳሌትና ተግባር የምንመራ አንድንሆን እርዳን፤ ምክንያቱም አንተ ብቻ የፍቅር ሁሉ ምንጭ የሆንክና ከአንተ ሌላ ምንም የተለየ ምንጭ የለም፤ ሌላው ሁሉ ውሸት ነው፤ ሁልጊዜም እናመሰግንሃለን ዛሬም ዘውትርም ለዘለዓለሙ አሜን!!

# ሃያ ስድስተኛ ቀን - Day 26

‹‹የዋሆች ብፁአን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና፡፡›› ማቴ 5፤5

‹‹Blessed are the meek for they will inherit the earth›› Matthew 5:5

የሰማያት አምላክ ሆይ ስምህ ሁል ጊዜ የተመሰገነ ነው፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል ልባችን ወደ መታሰቢያህ ለመሄድ ይናፍቃል ሁል ጊዜ ቀድሰኝ አእምሮዬም ለአንተ የተከፈተ ይሁን በአንተ ዘንድ የታወቅሁ ልሁን፣ መንፈሴንም በሰላምህ ሙላው ይህም ሰላምህ ከመታወቅና ከሃሳብህ ይልቅ ታላቅ ነው በነገር ሁሉ አንተ ላይ መደገፍን አስተምረኝ በአንተ ላይ የሚመኩ ሁሉ የተባረኩ ናቸው፡፡

በጠራሁት ጊዜ የሁሉ ጌታ ይሰማኛል፣ ምህረትህን በእኔ ላይ አድርግ፣ ፀሎቴን ስማ የደህንነቴ አምላክ ሆይ ትረዳኝ ዘንድ ናልኝ በድካሜ ተሸንፌአለሁ ኃጢያቴም በፊትህ ነች ራሴንም ሕይወቴንም በእጅህ ላይ አስቀምጣለሁ፣ ጌታ ሆይ በሕይወት መከራዎቼ ሁሉ አንተ ምራኝ፣ ኃይልህ ከሁሉም ነገር በልጦ ያልፋልና፣ አንተ የደካማውን ነፍስ ከአመጸኞች እጅ አድነሃል፣ ከከበበኝ ከክፉ ሃሳብ ሁሉ አድነኝ፣ የዘለዓለም ሕይወት ውሃ ወዳለበት፣ ስቃይ ፣ ርሃብ ፣ ሞት ወደሌለበት መንግስተ ሰማያትህ ውሰደኝ፣ ከአንተ ጋር መኖር ይሆንልኝ ዘንድ ነጩን ልብስህን አልብሰኝ የተቀደሰው ስምህ ሁል ጊዜ የተባረከ ይሁን አሜን፡፡

# ሃያ ሰባተኛ ቀን - Day 27

‹‹የሚያዝኑ ብፁአን ናቸው መጽናናት ያገኛሉና፡፡››
ማቴ 5፤4

‹‹Blessed are those who mourn for they shall be comforted›› Matthew 5:4

የተቀደስክ አምላኬ ሆይ ስላረግክልኝ መልካም ነገሮች ሁሉ አመሰግንሃሁ፡፡ አንተ ደግፈኸኛል ፣ ራሴንም ቀና አድርገህልኛል፣ እርግጠኛ እንድሆን በፍቅርህ አስተምረህኛል ፣ እንደገናም ንፁህ እሆናለሁ በንስሃና በይቅርታ መንፈስህ ሙላኝ ሁል ጊዜ በፊት ሆኜ ራሴን እንዳነፃና ኃጢያቴን ንድናዘዝ እርዳኙ የአንተን ታላቅነት፣ ጥንካሬና የትንሣኤህን ኃይል እንድገነዘብ እርዳኝ ጌታ ሆይ ደህንነት ከሰጠኸኝ ጊዜ ጀምሮ የሰጠኸን የሕይወት ዕቅድ አምነዋለሁ አንተ አልፋና ኦሜጋ ነህ መጀመሪያና መጨረሻ አንተ ነህ፣ የሚከተሉህም ሁሉ አይጠሙም፣አንተ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከሆንክ እንዴት እንጠማለን ? ጌታ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ ብለሃል፤ የአንተ እውነተኛ ተማሪ እንድሆን እርዳኝ ፣ በአንተ ለማመንና በቃል ኪዳንህ ለመታመን ራሴን አዘጋጃለሁ ፡፡ ፀሎቴን ስለሰማህ ሁል ጊዜ አመሰግንሃለሁ፣ እኔን ስለምታስበኝና በልብህም ስለሆንኩ እምነቴን ሁሉ በአን ልይ እጥላለሁ ስለ እኔ ከአንተ በቀር መልካም የሆነውን የሚያስብልኝ የለም፣ ከጨለማ አውጥተኸኝ ወደ እውቀት ብርሃንህ አስገባኝ በመንፈስህ ተጠጋኝ እጠበኝም መልካም የውሃ መያዣ አድርገኝ ክብርና ምስጋና ሁሉ ለአንተ ለዘለዓለም ይገባሃል አሜን፡፡

# ሃያ ስምንተኛ ቀን - Day 28

‹‹እኔ የአለም ብርሃኝ ነኝ፣ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም፡፡» ዮሐ 8፤12

<I am the light of the world. Wherever follows me will never walk in darkness, but will have the light of life.> Jhon. 8:12

ዓለምን በቃልህ የፈጠርህና እኔንም ከፍጥረታቶችህ መካከል ስለለየኸኝ ሕይወቴንም ሰለባረከህ አመሰግንሃለሁ፤ አንተ ከአብርሃም ጋር አብረህ የተጓዝህና የትውልድም አባት ያደረግኸው ነህ፤ ከአባቴ ከአብርሃም ጋር አብረህ እንደተጓዝህ ከእኔም ጋር ተጓዝ፤ እርሱንም እንደባረከህ ባርከኝ፤ ከአንተ ጋር የጠበቀ ግላዊ ግንኙነትን እንድለማመድ እርዳኝ አለማዬን በደንብ እንድረዳና እኔም በዚህ ምድር ላይ የሕይወትን ዓላማ እንዳከናውን ከእኔ ጋር ሁን፤ በአባታችን አብርሃም የሕይወት እርምጃዎች ውስጥ መራመድን እፈልጋለሁ፣ እርሱም በአንተ አምላካችን ምሬት የሄደና ፍቃድህን ሁሉ በታማኝነትና በእምነት የፈፀመ ሰው ነው፡፡ ቀን በቀን እምነቴን እንዳሳድግ እርዳኝ፤ ቤተሰቤን በእጅህ ለአንተ አስረክባለሁ ለእነርሱም በረከት እንድሆን እርዳኝ፣ በሁሉም ደረጃ ላይ ያለውን ፍላጎታችንንና መንፈሳዊ ረሃባችንን አሟላልን፤ ወደሕይወት ማረፊያ ሊያቀርበን የሚችለውን መንፈሳዊ ሕይወት ምንጭ ምሬቱን ስጠን፤ ምክንያቱም ዘለዓለማዊውን ሕይወት ከአንተ ጋር መሆንን እንመኛለንና ዘለዓለማዊ የተወደድክ እግዚአብሔር ሆይ ስለነበርኩበት የሕይወት ውድቀቶች ሁሉ እናዘዛለሁ፤ እነርሱንም ላለመድገም ቆርጫለሁ፤ የኃጢአትን ይቅርታ ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ በአጠገብህ ሆኖ የሚማልድልኝና ለኃጢአቴ ይቅርታ እንዳገኝ የሚለምንልኝ አዳኝ ስለሰጠኸኝ ሁልጊዜ አመሰግንሃለሁ፤ አሜን!

# ሃያ ዘጠነኛ ቀን - Day 29

‹‹በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፤ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል» ዮሐ 10፤9

<I am the gate whoever enters through me will be saved. They will come in and go out and find pasture..> Jhn. 10:9


አምላኬ ሆይ አንተን ለማወቅ ስለሰጠኸኝ እድል አመሰግንሃለሁ፤ የሕይወት አጋጣሚዎች ነፍሴን አስጨንቋታል፤ ያለፉት አመታት ድርጊቶችና ቁስሎች በሕይወቴ ላይ ምልክትንና ጠባሳ ትተውብኛልና፣ በውስጥ ሕይወቴም አምሮዬን አስጨንቆኛልና፣ ጌታ ሆይ ካለፉት ሁኔታዎች ቀንበር ነፃ አውጣኝ፤ ባለፉት ከነበሩት ድርጊቶች ነፃ ወጥቻለሁ፤ ያለፉት የሆኑት ነገሮች አልፈዋልና አንተንና ቃልህን በማወቃችን ከአንተ ጋር በብርሃን መሆን ችለናል፤ በዚህም የአምላኬን እውነተኛ ኃይል ማወቅ ችያለሁ፤ የሰው ህይወት ምንኛ አንተን ትፈልጋለች አንተ ተስፋዬ ነህና፣ ሉአላዊ የሆንከው አምላክ ከወጣትነቴ ጀምሮ ትምክህት ሆነኸኛልና፤ ከመወለዴ ጀምሮ በአንተ ላይ መመካት ሆኖልኛል፤ ከእናቴ ማህፀን ውስጥ ወደ ሕይወት አመጣኸኝ፤ ሁልጊዜም አመሰግንሃለሁ፣ አንተ ፈዋሽ አምላክ መሆንህ የታወቀ ነው፤ ወደ አንተም ስመጣ ካለፉት ቁስሎቼና አስቸጋሪ ወቅቶች እንዲሁም ከአለም መገፋት ለመዳን ወዳንተ ቀርቤአለሁ፤ እኔንም ስለመለስከኝና በአንተ የተሞላ መቅረዝ ስላደረግኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ይህም አንተ ለዓለም ያለህን ፍቅር ያሳያልና እስከ ዘለዓለሙ ለዘወትር ተመስገን፤ አሜን!!

# ሠላሳኛ ቀን - Day 30

‹‹እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ በሰጎ እንዲደረግ እናውቃለን» ሮሜ 8፤28

<And we know that in all things God works for the good of those who love him, who have been  called according to his purpose.> Rome. 8:28

ጌታ ሆይ ስለአዲሱ ቀን እና አዲስ እውቀት አመሰግንሃለሁ፤ ነፍስንና መንፈስን ስለሚያጠግበው አዲስ ስጦታህ አመሰግንሃለሁ ስጦታህ ልብን ያበለፅጋል፤ ሁለመናንም ይሞላል ርሃብንም ያጠግባል፤ ፍላጎትንም ያሟላል፤ እኛ ጌታ ሆይ ምንፈሳዊ ሙላትንና ደስታን የሞላ ሕይወት እንሻለን በዚህ ዘመን ረሃብ መንፈሳዊ ጉድለት፤ ስሜታዊና የኑሮ መጓዳል በእጅጉ እየበዙ ነው ስለሆነም እራሳችንን እንድንቆጣጠርና አንተንም በማወቅ አንድንረካ እርዳን፤ ከመንፈስህ ጋር እንዴት እንደምንተባበር አሳየን፤ በቅድስና እና እራስን ዝቅ በማድረግ እንዲሁም ያለንን ነገር ሁሉ በፀጥታና በመዋረድ ለመያዝ እንድንችል እርዳን፤ ጌታ ሆይ መንገድህን አስተምረን፤ የዘለዓለም ሕይወትን ከሚሰጠው የሕይወት ውሃህ እንድንጠጣ እርዳን፤ ዓለም እንደዚህ ያለ ሕይወት አትሰጠንም በመቅደስህ ውስጥ እንድንቀመጥና አንተን እና አንተን ብቻ እንድናይ በሕይወትህ ስጦታ ሙላን፤ ከአንተ በቀር ርሃባችንን ሊያረካ የሚችል ነገር የለም እና አንተ ብቻ እንዴት በሕይወት እንደምትሞላን እና የነብሳችንንም ፍላጎት እንደምታሟላ ታውቃለህና፤ የተቀደሰው ስምህን ለዘለዓለም እንባርካለን፤ አሜን!!


WHEN YOU NEED A MIRACLE
IN YOUR LIFE
PRAY
TO
GOD
I ALWAYS ASK GOD
የ30 ቀናት ፀሎት